ሞረሸ ወገኔ የዐማራ ድርጅት (ሞወዐድ)
Moresh Wegenie Amara Organization (MWAO)

Website: www.moreshwegenie.org E-mail: InfoAndPR@moreshweg...

ትግላችን ትውልድ ተሻጋሪ ነው። የዐማራው መደራጀት የኅልውናው እና የማንነቱ መሠረት ነው።
Our struggle is trans-generation. Amara’s organization is the basis of its existence and identity.

*ሞረሸ ወገኔ የዐማራ ድርጅት* *ሰኞ፣ ኅዳር 30፣ ፪ሺ ፲፫ ዓ.ም. (Nov. 30, 2020)* *ቅጽ ፯ ቁጥር ፷፫*

# በተባበረ መስዋዕትነት በወያኔ ላይ የተገኘን ድል ጠብቆ፣ ኢትዮጵያ የዜጎቿ ሁሉ የፍትህና እኩልነት ሀገር እንድትሆን ፈጣን መዋቅራዊ ለውጥ ያስፈልጋታል!

የትግራይ ነፃ አውጭ ግንባር (የትግሬ-ወያኔ) ዘረኛ አገዛዝ ኢትዮጵያንና ኢትዮጵያዊነትን ለማፍረስ ዓልሞ፣ ለዓላማው ማስፈጸሚያም በቋንቋ ልዩነት ላይ በተመሠረተ፣ ዐማራ ጠል ሕገ-መንግሥት አውጥቶ፤ ኢትዮጵያዊነትንና ዐማራን ከምድረገፅ ለማጥፋት ለዘመናት ሰርቶበታል። በጥላቻ፣ በዘርፊያና በወንጀል ላይ የተገነባው የወያኔ የሸፍጥ ፖለቲካ ዛሬ በራሱ በወያኔ ላይ እንደእባብ ተጠምጥሞ እየነደፈው፤ የመጨረሻ እስትንፋሱ በሲቃ ተሞልታ በስቃይ ላይ ይገኛል።

ነገር ግን “ያዳቆነ ሰይጣን ሳያቀስ አይተውም” እንዲሉ እሞት አፋፍ ላይ እያለም ወያኔ “ሳምሪ” የሚል ገዳይ ድርጅት አደራጅቶ ማይካድራ ላይ እስከአሁን አስከሬናቸው በተገኘው ብቻ ከ700 በላይ ዐማራ አስጨፍጭፎ ገድሎ ብዙዎችን አካለጎደሎ አድርጓል። በዚህም ሳያበቃ አሁንም ወያኔ ያሰበውን ያህል ባይሳካለትም በተደጋጋሚ ሚሳይል በማስወንጨፍ ጎንደርንና ባህርዳርን ለማውደም ሙከራ አድርጓል።

ወንጀለኛው ወያኔ በኢትዮጵያ የመከላከያ ሰራዊት ላይ የፈፀመው ግፍ ለግብአተመሬቱ መፋጠን ከፍተኛ አስተዋፅዖ አድርጓል። ግፈኛውን ወያኔ ለመቅጣት ከኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ባልተናነሰ፣ አከርካሪውን ሰበርኩት፣ አጠፋሁት ሲለው የኖረው የዐማራ ፋኖ፣ ልዩ ኃይልና ሚሊሽያ፣ እንደዘውጌዎች በደል ሳይሆን በኢትዮጵያዊነቱ ድርድር የማታውቀው የዐማራ ገበሬ ሳይቀር ጥቃት የተፈፀመበትን የኢትዮጵያ መከላከያ ሰራዊት ለማዳንና አገሩን ለመታደግ ዘምቶ በከፍተኛ ተጋድሎ አኩሪ ድል ከማስመዝገቡም በላይ፤ እብሪተኛውና ወራሪው ወያኔ የዘረፈውን የዐማራ አፅመ ርስት ወልቃይት፣ ጠገዴ ሁመራ፣ አላማጣ ራያ ወዘተን ደሙን አፍስሶ አጥንቱን ከስክሶ አስመልሷል። የመከላከያ ሰራዊታችን ግዳጅን በሚገባና በድል እየተወጣችሁ እንደሆነ በተግባር አስመስክርችኋል። ስለኢትዮጵያዊነት ክብር ውድ ህይዎታችሁን ሰውታችሁ ለዚህ ስላበቃችሁን ክብር ይገባችኋል።

የዐማራ ጦር ከጀግንነቱ ጎን ለጎን ስለሰብዓዊነቱም የጦር ሜዳ ጓዶቹና ምርኮኞቹ ስለመሰከሩለት ወገኑንና ታጋሹን የዐማራ ህዝብ አኩርቷል። ዱሮም ዐማራ በባህሉ ሴት፣ ለአቅመ አዳም ያልደረሱ ህፃናት፣ ሽማግሌና አሮጊት መግደል ነውር እንደሆነ በሚገባ ያውቃል። ዐማራ በወታደርነት ተግባር ላይ ተሰማርቶ እያለም ቢሆን በፊት ለፊት የመጣን ጠላት ገጥሞ ያሸንፋል እንጅ የተማረከ ሰው ጠላትም ቢሆን ይንከባከባል እንጅ አያንገላታም። ወትሮም ዐማራ በሌሊት ሄዶ የተኛ ቤተሰብ አያጠቃም። ለዚህም ስነምግባራችሁ የሞረሸ ወገኔ የዐማራ ድርጅት አድናቆቱን በኩራት ይገልፃል።

የሞረሸ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ለጀግናው የዐማራ ጦር እንኳን ደስ አላችሁ፣ እንኳን ደስ አለን እያለ፣

- |**ለዐማራ ልዩ ኃይል፣ ፋኖና ሚሊሽያ፤** አጥንታችሁን ከስክሳቸው ደማችሁን አፍስሳችሁ ያስመለሳችሁትን የዐማራ አፅመ እርስት በክብር፣ በጥንቃቄ ትጠብቁት ዘንድ ታሪካዊ አደራና ኃላፊት አለባችሁ። በደም ያስመለሳችሁትን አፅመ ርስትና በብቃት ያገኛችሁትን ድል ከዐማራ ህዝብ ጋር በመሆን በንቃት የምትጠብቁበት ሰዓት አሁን ነው። በተለይ ጠ/ሚ አብይ አህመድ በትግራይ ሥራ አስፈጻሚ አድርገው የሾሟቸው ግለሰብ የሚሉትን ስንሰማ፤ የኦሮሞ ብልፅግና ልሳን በሆነው በኦሮሞ ብሮድካስቲንግ ኔትዎርክ (OBN) እየተቀነቀነ ያለውን የዐማራ ህዝብ እርስት የሆነውን ራያን የኦሮም ለማድረግ የሚያስተላልፉትን ፕሮፓጋንዳ ስናዳምጥ፤ በኦሮሞ የሰራዊት

መሪዎችና ሌሎች የጠ/ሚሩን አመለካከት ይገልጻሉ የሚባሉ ሰዎች የሚያስተላለፉትን መልዕክትም ላጤነ ሰው፤ በወልቃይት ጠገዴ፣ ጠለምት፣ ራያ፣ አላማጣ ወ ዘ ተ ያሉ ዐማራዎች በመስዋዕትነት ያገኙትን አፅመ እርስት አለማክበር ያለ ይመስላል። ይህ አያያዝ ከፍተኛ የህዝብን ንቀት የሚያሳይ ነው። ይህ በኦሮሞ ብልጽግና መራሹ መንግስትና በአጃቢው ብአዴን/ ዐማራ ብልጽግና ዐማራውን ደግሞ ደጋግሞ መካድና ለሌላ ዙር ጦርነቶች የሚዳርግ ኃላፊነት የጎደለው እሳቤ በጊዜ ሊቋጭ ይገባል። በአንፅሩ ጉዳዩን በአንክሮ በማጤን፤ ለፋኖና ለዐማራ ሚሊሺያ፣ በአጠቃላይም የዐማራ ህዝብ ተገቢውን አቅም መገንባትና የስነ ልቦና ዝግጅት ማድረግ ይገባዋል። ዐማራው ማንነቱን፣ ህልውናውን፣ የዜግነት መብትና ጥቅሙን፣ የሀገር ገንቢነት ሚናውን፣ ወዘተ ሊያስከብር የሚችለው በራሱ መስዋእትነትና ትግል እንጂ ማንንም በመለመን በምጽዋት የሚሰጠው አለመሆኑን መረዳት ተገቢ ነው።

- **ለወገናችን የአገው ህዝብ፣** በዚህ ወያኔ በፈጠረብን የከፋፍለህ ግዛው ዘመን፣ ሁሉም ዐማራ ላይ እጁን እንዲያሳርፍ በሚቀነቀንበት ወቅት፣ የጎጠኖቹን አካሄድ ወደጎን በመተው የትኛውም ቅስቀሳ ሳይበግራችሁ፤ ታሪካዊ አንድነታችሁን አፅንታችሁ፤ በመካከላችን ደም ሳይፈስ በትዕግስትና በፅናት ስለቆያችሁ፣ ክፉውን ቀን ሁሉ በመተከል በጋራ አብረን እየሞትን በጋራ ስለተሻገርነው ከሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ምስጋናችን ይድረሳችሁ። እንዲሁም ወያኔ ተወግዶ ለተሻለና ተስፋ ለተጠለበት ቀን በመድረሳችን እንኳን ደስ አላችሁ።
- **ለአዴፓ፣ የዐማራ ብልፅግና፤** ለሰላሳ አመት ከዐማራ ጠሎች ጋር በመተባበር ዐማራን ብዙ የህይወት ዋጋ እንዳስከፈላችሁ ይታወቃል። ዛሬ ግን ወያኔ በመጨረሻው ሰዓት በሰራችው ወንጀል የዐማራው ልዩ ኃይልና ሚሊሻ እርስቱን እንዲያስመልስ ትብብር በማድረጋችሁ ልትመሰገኑ ይገባል ። ነገር ግን አሁንም ከታሪክ ተወቃሽነት ለመዳን ከአለፈው ስህተት በመማር ይህ በቋንቋና በነገድ የተመሰረተ ህገመንግሥት ተቀይሮ የኢትዮጵያ ህዝብ፣ በተለይም የዐማራን ህዝብ የሚመጥን፣ ኢትዮጵያውያን ያለምድልኦ የሚያስተናግድ ህገመንግስት እንዲኖር እንድታደርጉና ጥፋታችሁን እንድታካክሱ ጥሪያችን ይድረሳችሁ። በተለይ በቀበሌና በወረዳ ደረጃ ያላችሁና ለወገናችሁ ቅርብ የሆናችሁ የአዴፓ አባሎች በሙሉ የድርጅታችንሁን የዐማራ ጠሎች አገልጋይ ዱላ በመሆን ያለፈውን ጊዜ በቁጭት በመመልከት፣ በተለያዩ ጊዜያዊ ጥቅም በመደለል ወገንና ሀገር የምንበድልበት ጊዜ መቆም አለበት በሚል፣ በቃ ብላችሁ፣ ወያኔን እንደ ድርጅት ማጥፋት ብቻ ሳይሆን፣ ዐማራን በጠላትነት የፈረጀውና ወያኔ እውን ሆና እንድትቀጥል የሚያደርገውን ሕገመንግስት ተቀይሮ፣ ቆመንለታል የምትሉት ዐማራ በመላው ኢትዮጵያ የዜግነት መብቱ ተጠብቆ በሰላም መኖር ይችል ዘንድ በማገዝ ታሪካዊ ኃላፊነታችሁን በመወጣት ካሱት። እራሳችሁንም ከህሊና ቁስል አድኑ፣ በማለት ወገናዊ ጥሪያችንን እናስተላልፋለን። ተጠሪነታቸውና ተግባራዊ እንቅስቃሴያቸው እንወክለዋለን ለሚሉት ዐማራ ሳይሆን በተረኝነት የሚኒሊክን ቤተመንግስት ለተቆጣጠረው አካል አገልጋይ የሆኑ የድርጅታችሁን አመራሮች አስወግዳችሁ እራሳችሁንና ድርጅታችሁን ነጻ አውጥታችሁ ለወገናችሁ እንድትቆሙ ልባዊ ምክራችንን እናቀርባለን።
- **በዶ/ር አብይ አህመድ የሚመራው ብልፅግና፤** በጎጥ ላይ የተመሰረተ ከፋፋይ ፓለቲካ፣ ከልክ ያለፈ ጥላቻና ስግብግብነት ወያኔዎችንም ስላልጠቀመ፤ ወያኔዎችን የተጠናወታቸው ተንኮል፣ ጭካኔና ዝርፊያ የኋላ ኋላ ለውድቀት ስለዳረጋቸው፤ ከወያኔ ውድቀት ተምራችሁ፣
    1. ህገ መንግሥቱን ኢትዮጵያዊ ይዘት ወዳለው ህገመንግሥት በመቀየር፣ ሰላምና መረጋጋትን እንድታሰፍኑ፣
    2. ወያኔና ኦነግ ከ1983 ዓ/ም ጀምሮ እስከአሁን ከፈፀሙት ብዙ የዘር ማጥፋትና ሌሎች ወንጀሎች አንጻር፣ ሁለቱም ድርጅቶች በሽብርተኝነት እንዲፈረጁ፤ ወያኔና ኦነግ በሽብርተኝነት ከተፈረጁ በኋላ በሽብርተኛ ስለመሆናቸው በዓለም ታውቀው እንዲመዘገቡ በማድረግ፣ ለአንድ ጎጥ ብቻ ሳይሆን የኢትዮጵያን ህዝብ የሚመጥን አስተዳደር እንድታዋቅሩ፣
    3. ከ 1983 ዓ ም ጀምሮ እስከአሁን ድረስ በመላው ኢትዮጵያ ስለተፈፀመው የሰብዓዊ መብት ጥሰት፣ የዘር ማጥፋትና የህዝብ ጭፍጨፋ፣ ቤት ንብረት የማውደምና የማፈናቀል ስራ በተለይም የዐማራ ህዝብ በፓሊሲ ተቀርፆ ለደረሰበት በደል ሁሉ ገለልተኛ አጣሪ ኮሚሽን ተቋቁሞ እንዲጠራ፤ ወንጀሉ ከተጣራ በኋላ ወንጀለኞች ለፍርድ እንዲቀርቡ፣ በደል የተፈፀመባቸው ተጎጅዎች ፍትህና አስፈላጊው ካሳ እንዲከፈላቸው ፣ የተፈናቀሉ ኢትዮጵያውያን ሁሉ ወደነበሩበትና ወደወደዱት ቦታ ሄደው እንዲኖሩ እንድታደርጉ እንጠይቃለን።

ይህን ባለማድረግ፣ የሀገር ህልውና ለማስከበር በማለት ወያኔን ከትግራይ ነቅሎ ለመጣል የተደረገው ጦርነት፣ የዐማራው ልዩ ኃይል፣ ፋኖና የዐማራ ሚሊሽያ ከኢትዮጵያ ሰራዊት ጋር በጦርነቱ ላይ ያደረጉትን ማስዋዕትነት የሚያሳንስ መሆኑ መታወቅ አለበት። የወያኔ የፖለቲካ ፕሮግራም ተሸካሚ የሆነውን የአፓርታይድ ሕገ መንግሥት በኢትዮጵያ ላይ እስካለ ድረስ የሀገር ህልውና፣ ውስጣዊ ሰላምና አንድነት፣ የዜጎች እኡልነት ፍትህን ማምጣት በፍጹም አይቻልም። የዜጎች እኩልነት፣ ሰላም፣ አንድነት፣ ፍትህ የማይረጋገጥበትን የአፓርታይድ መዋቅርና የዘር ፖለቲካ ተሸክሞ ብልጽግናን አመጣለሁ የሚባለው ማንንም ሊያሳምን ስለማይችል፤ የህዝብን ፍላጎትና ተስፋ እውን ማድረጉ ላይ እንድትሰሩ እንጠይቃለን። እንደስማችሁ “ብልፅና ፓርቲ” የበለፀገች ኢትዮጵያን የምትመኙ ከሆነ ያገኛችሁትን ታሪካዊ እድል ተጠቅማችሁ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የከፋፋይ ፓለቲካን አስወግዳችሁ ለኢትዮጵያ ህዝብ የሚጠቅምና ሰላምን የሚያሰፍን ስራ እንድትሰሩ ልናሳስባችሁ እንወዳለን።

- **ለኢትዮጵያ ህዝብ፣** የዐማራ ህዝብ መቸም ቢሆን ሌላውን ዘር ወይም ነገድ በጥላቻ የማያይና ከሁሉም ወገኖቹ ጋር ለዘመናት ያካበታቸውን የጋራ እሴቶቹን መሰረት አድርጎ በሰላም፣ በመተባበር፣ በመከባበርና በአንድነት አብሮ የኖረ መሆኑን ሁሉም የሚያውቀው ሀቅ ነው። የዐማራ ህዝብ በሕገ መንግሥትና በፖሊሲ ተቀርጾና ብቸኛ ጠላት ተደርጎ በማንነቱና በህልውናው ላይ ያነጣጠረ አሰቃቂ በደል እየደረሰበት ነው። የዐማራ ትግል የተቃኘው እየደረሰበት ያለውን እልቂት፣ ከፊቱ የተጋረጠውን አደጋና በደል ለማስቆምና መሰረታዊ ለሆነ ሰብዓዊ መብት የማስከበር ትግል ነው። የዐማራ ህዝብ ግቡ ከአድልዖ የፀዳች ኢትዮጵያን ማስቀጠል ስለሆነ ዘላቂ ግቡ የሁሉም ዜጎች ግብ ነው። ይህም ማንነትን ማለትም ዘርና ሀይማኖት መሰረት ካደረገ ፓለቲካ ነጻ መሆን ማለት ነው። ሁሉንም ዜጋ በእኩልነት የሚያይ ሥርዓት እውን ሆኖ፣ ማንኛውም ዜጋ በየትኛውም የኢትዮጵያ ምድር ከማንም ጫና ሳይኖርበት በመረጠው ቦታ ሰርቶና ነግዶ እንዲኖር በህግ የተደገፈ መብት እንዲኖረው ይገባል። ከምንም በላይ እያንዳንዱ ዜጋ ሰብዓዊ መብቱ የሚከበርባት ሀገር እንድትሆን፣ ስራና ስልጣን በነገድ ማንነት ሳይሆን በችሎታ እንዲሆን የምንመኛትን ኢትዮጵያ በጋራ መገንባት ይኖርብናል። ለዚህ እውን መሆን ዐማራውን በጠላትነት የፈረጁ አካሎች ኢትዮጵያን በማድከምና በአፓርታይድ የከፋፍሎ መግዛት ፈሊጥ በህዝብ ስቃይና ለከት ያጣ ዘረፋ አትራፊ በሆኑበት የ30 ዓመታት ጉዞ በቃ ብለን ከላያችን ላይ ማሽቀንጠር ይኖርብናል። ሰላም፣ ዲሞክራሲ፣ አንድነትና፣ እድገት የሚረጋገጥባት ሀገር እውን ለማድረግ በጋራ እንታገል ሲል የሞረሽ ወገኔ የአማራ ድርጅት ጥሪውን ያቀርባል።
- **ለተቀዋሚ ፓለቲካ ድርጅቶች፣** ተቀዋሚ ፓርቲ የሚያስፈልገው መንግስት በወደደውና በፈቀደው ብቻ ለመንቀሳቀስና ለገዥው ፓርቲ ፍላጎት ወይም ጫና አጎንባሽ ሆኖ የእይታ ምርጫ አሟሟቂ ለመሆን አይደለም። የተቀዋሚ ድርጅቶች ለህዝብና ለሀገር የሚጠቅም የራሳቸውን አማራጭ የፖሊሲ ሀሳቦች ይዞ በመቅረብ ከገዥው ፓርቲ የሚለዩበትን በግልጽ በማስቀመጥ የሚታገሉ መሆን አለባቸው። ለሀገር የሚጠቅም ፓለቲከኛ ተቃውሞውም ሆነ ድጋፉ በመርህ መሆን አለበት። የዘር ማጥፋት ወንጀሎች ላይ እንኳን መስማማት ያልተቻላችሁ የመርህ አለባነት መንገስ የፈጠረው ችግር ነው። ስለዚህ የተቃዋሚ ፓርቲዎች ከወያኔ ውድቀት በኋላ ለኢትዮጵያ የተሻለ አመራርና አስተዳደር እንዲኖር፣ የዜጎች መብት እንዳይጣስ ቁርጠኝነት ሊኖራችሁ ይገባል። 30 ዓመታት ያስቆጠረው የዘር ጭፍጨፋዎች ዘመን ዋና መሰረቱ የአፓርታይድ ህገ መንግሥቱ ስለሆነ ይህን ለማስቀየር እንድትተጉ እናሳስባለን። ከገዥው ፓርቲ ጋር የተለየ አቋም ስላላቸው ብቻ ለእስር ተዳርገው፤ ፍትህ አጥተው የሚሰቃዩትና በኢትዮጵያዊነት ላይ ባማይደራደሩት የተቃዋሚ ፓርቲ አባሎች እንዲፈቱ የበኩላችሁን ጥረት እንድታደርጉ፣ ሞረሽ ወገኔ የዐማራ ድርጅት ጥሪውን ያቀርባል።

አንድ ዐማራ ለሁሉም ዐማራ፤ ሁሉም ዐማራ ለዐንድ ዐማራ!

ፈለገ አሥራት የትውልዳችን ቃል ኪዳን ነው!